

በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከኤፕሪል 11-20 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

# ከኤፕሪል 21-30 እና ከሜይ 1-10/2025 የሚኖረው የአየር

# ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኤፕሪል 2025

አዲስ አበባ

## 1. እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ


ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምዕራቅ፣ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ስድስት ቀናት የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ በመካከለኛው፣ በደቡብ ምስራቅ እና በምዕራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲሰ አበባ ቦሌ 18.5፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 21.4፣ በአርባምንጭ 39.7፣ አዋሳ 10.9 ፣24.5፣ 42.0፣ ደብረ ማርቆስ 16.6፣ ቢሾፍቱ 18.6፣ ጎዴ 13.6፣ ጎንደር 15.9፣ ጅማ 16.5፣ 11.3፣ መተሃራ 14.8፣ 18፣ ነገሌ 27፣ 16.5፣ 27.0፣ 20፣ ሮቤ 20፣ 18.2፣ 34.7፣ አቦምሳ 26.4፣ 24.4፣ 33.5፣ አደሌ 13.6፣ አዴት 12.4፣ አደዋ 12.4፣ አዲግራት 25.5፣ አይደር 14፣ አይራ 15.2፣ ሐሮማያ 14.5፣ አለም ከተማ 20.5፣ 32.5፣ አማን 50.2፣ አምባ ማሪያም 14.8፣ 12.4፣ አምቦ 13፣ 35.5፣ 38.9፣ አንገር ጉቲን 30.2፣ አርጆ 18.4፣ 10.2፣ 16.6 24.2፣ አርሲ ሮቤ 19፣ 12.2፣ 47.2፣ 17.4፣ ባቲ 11፣ በደሌ 13፣ ብላቴ 16፣ 24.9፣ 16.7፣ ቦሬ 18.9፣ 41.5፣ 17.8፣ 34.8፣ 12.2 31.9፣ 26.5፣ ቡሂ 34፣ 55.6፣ ቡሬ 25፣ ቡረጂ 23፣ 11.5፣ 15፣ 15.4፣ 33.6፣ ጨፋ 42.1፣ ደባርቅ 19.1፣ ደብረ ብርሃን 10.6፣ ደብረ ወርቅ 10.5፣ ደምቢ ዶሎ 36.2፣ 21.8፣ 12.5፣ ዲላ 10.2፣ 50.2፣ 49.2፣ 27.5፣ 11.8፣ ዶሎ መና 10.2፣ 20.1፣ 10.2፣ ኢጃጂ 37.6፣ 14.5፣ እነዋሪ 10.8፣ ፊቼ 26.8፣ 11.9፣ ጋምቤላ 10.1፣ ጋቲራ 10.1፣ 22.4፣ ገለምሶ 12.2፣ ግዋኔ 17.0፣ ወሊሶ 25.1፣ ጊዳ አያና 11.3፣ ጊኒር 31፣ ጉንዶ መስቀል 38.5፣ 31.7፣ ቡሌ ሆራ 12.6፣ 20፣ ሐረር 12.9፣ ሆሳዕና 63.8፣ 19.፣ እምድብር 18.4፣ 12.3፣ 22.6፣ ጃራ 31.3፣ 11.5፣ ጂንካ 46.7፣ 19.9፣ 16.5፣ 14.6፣ ካቺሴ 16.2፣ 17.3፣ 48.1፣ ቀብሪ ዳር 16፣ 36፣ 20 ፣18፣ ኮንሶ 17.7፣ 13.2፣ 24፣ 14፣ ቁሉምሳ 13.2፣ 17.2፣ ሊሙ ገነት 55.1፣ 13፣ ማጀቴ 13.3፣ ማጂ 15፣ 27፣ 11.2፣ 31.5፣ 26.3. 20.6፣ መኤሶ 24.1፣ 13.1፣ መካነ ሰላም 25.5፣ ምዕራብ አባያ 19.4፣ 19፣ ሞጣ 11.5፣ ሞያሌ 27፣ 91.5፣ አዳማ 58.8፣ 14፣ ንፋስ መውጪያ 16.6፣ ኑራ ኤራ 11.1፣ 35.7፣ ሳዉላ 25.2፣ 13.5፣ 15.4፣ 11.6፣16.4፣ ሰኮሩ 43፣ 44.8፣ ሰንቃጣ 12.9፣ ሽሬ 15.8፣ 15.9፣ ሲሪንቃ 15.6፣ 40.4፣ ቴፒ 50.2፣ 21.4፣ 41.2፣ ተርጫ 37.7፣ 34.9፣ 19.7፣ 27.6፣ ወገል ጤና 21፣ 21.6፣ ወራቤ 29.3፣ ወላይታ 11.1፣ 19.3፣ 18.2፣ 25.6፣ 14.8፣ ያቤሎ 20፣ 16.4፣ 10፣ 15.1፣ 11.3፣ የትኖራ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

11.6፣ 38.7፣ 24.1፣ ባቱ 55፣ ጨለንቆ 13.6፣ 23.8፣ 1001.2፣ ዶሎ ኦዶ 29.2፣ ገርቦ 40፣ ሃመሮ 10.4፣ 20.0፣ ሃርሲሲ 22፣ ሂርና 19.2፣ ካራሚሌ 15.9፣ 34.8፣ 44.4፣ ቁሉቢ 28.8፣ ሽላቦ 24.5፣ አቃስታ 21.5፣ 15፣ ደበር ሲና 17.3፣ 27.7፣ 18.1፣ ደጋን 25.3፣ ጋሸና 17.5፣ ከሚሴ 14፣ ወግዲ 25፣ ተልተሌ 90.8፣ ጨፌ ዶንሶ 54.3፣ አቃቂ 25.1፣ ወለንጭት 33.3፣ እንዲሁም ቆቃ 24.2 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ40 የሀገሪቱ አከባቢዋች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የበልግ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50.2-101.2 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ጨለንቆ፣ ሞያሌ፣ ተልተሌ፣ ሆሳዕና፣ አዳማ፣ ቡሂ፣ ሊሙገነት፣ ባቱ፣ ጨፊ ዶንሳ፣ አማን፣ ቴፒ፣ ዲላ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡





ምስል፡1 ከኤፕሪል 11-20 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ አማሮ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ ዞኖች ፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሀዲያ፣ የሃላባ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ የጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ የደቡብ፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ዶሎ ኦዶ፣ ጃረር፣ ፋፈን፣ ኖጎብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የመካከለኛዉ ጎንደር ዞኖች፣ ደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፤ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ፣ ከአፋር ክልል የጋበ፣ ማሂ፣ ላይ ከ21-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ አማሮ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሀዲያ፣ የሃላባ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ የጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ የደቡብ፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ዶሎ ኦዶ፣ ጃረር፣ ፋፈን፣ ኖጎብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ፣ የሰሜን፣ እና የመካካለኛዉ ጎንድር ዞኖች፣ ደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፤ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራይ፣ ከአፋር ክልል የጋበ፣ ማሂ፣ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

በሌላ በኩል በመተሃራ፣ በአቦቦ፣ በፉኙዶ፣ በመተማ፣ በገዋኔ፣ በጋምቤላ፣ በሰመራ፣ በአዋሽ አርባ፣ በጊውን፣ በጎዴ፣ በፓዌ፣ በድሬ ደዋ፣ በኑራኤራ፣ በቀበሪዳሀር፣ በአይሻ፣ በሸዋ ሮቢት፣ በጨፋ፣ በጨዋቃ፣ በአዳማ፣ በቻግኒ፣ በቴፒ፣ በአቦምሳ፣ በአሶሳ፣ በሊሙገነት እና በብላቴ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 33.0 እስከ 42.2 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኤፕሪል ሁለተኛዉ አስር ቀናት በአብዛኛው የበልግ አብቃይና እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በተለይም በደቡብ፣ በመካከለኛው፣ በደቡብ ምስራቅ እና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን በማሻሻል ቀደም ብለዉ ተዘርተው በቡቃያ ደረጃ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች እድገት እንዲሁም ለመኸር ተጠቃሚ አካባቢዎች ለማሳ ዝግጅትና እንደ በቆሎ እና ማሽላ የመሳሰሉ የረዥም ግዜ ሰብሎችን ለመዝራት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እና ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው። በሌላ በኩል በከምባታ ዞን ዳምቦያ ወረዳ በነበረዉ ንፋስ በቀላቀለ ከፍተኛ ዝናብ በጉልባና ህዳሴ ሁለተኛ ደረጃ ት/ት ቤት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል (ካርታ 5) ፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኤፕሪል ሁለተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን፣ በላይኛው እና በመካከለኛው አባይ፣ አዋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው ዋቢ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል እንዲሁም በመካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በታችኛው ኦሞ ጊቤ እና ስምጥ ሸለቆ በጣም ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን ይህም እርጥበት ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት አዎንታዊ ሚና እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በአንጻሩ የተቀሩት ተፋሰሶች በተለይም የአባይ፣ የአዋሽ፣ የባሮ አኮቦ እና የላይኛው ምስራቃዊ ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ+2511155383944ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2. መግቢያ

የበልግ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው በኤፕሪል የሚዘነበው ዝናብ ነው። ስለሆነም የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ትግራይ፣ ምስራቅ አማራና ሱማሌ አካባቢዎችን ጨምሮ ከ70-120 ሚ.ሜ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚጨምር በመሆኑ ከ10-20 ለሚደርሱት ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ማለትም የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና ሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ ለ10 ቀናት ያህል እስከ 70 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል። በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በሲዳማ ክልል እና ደቡብ ኦሮሚያ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከ161-260 ሚ.ሜ ለ20 ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በተጨማሪም ከበልግ ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በኤፕሪል ወር በአብዛኛዉ የደቡብና የምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከ40% እስከ 50% የሚደርስ የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ። በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ በልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ እስከ አፕሪል የመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፣ በተጨማሪም ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ጋር ተያይዞ ወቅታዊው ዝናብ ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በኤፕሪል የመጨዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በምስራቅ፣ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-30, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ጨምሮ የደቡብ ምዕራብ እና የምዕራብ እንዲሁም የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ (ከ1-29 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ ፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት ቀናቶች ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና የሚያገኙት የዝናብ መጠን

| ክልል | ዞን | የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ባሌ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| | ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ | ቀላል መጠን (እስከ 10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ አማሮ፣ ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሌ፣ ባስኬቶ፣ አሪ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ነጎብ፣ ኤረር፣ ጃራር ፋፈን እና ዶሎ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ እና የመካከለኛዉ ጎንደር ዞኖች፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| | የሰሜን እና የምዕራብ ጎንድር፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ | ቀላል መጠን (እስከ 10 ሚ.ሜ) |




ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| | | |
|---|---|---|
| ትግራይ | የሰሜን ምዕራብ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| | የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ ዞኖች | ቀላል መጠን (እስከ 10 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (እስከ 10 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ | ቀላል መጠን (እስከ 10 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኙዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬደዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |

## 2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በበልግ ወቅት በመደበኛነት ትኩረት ከሚሹ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መካከል ቀን ላይ የሚኖረው የሙቀት መጠንና ሌሊት ላይ ደግሞ የሚታየው ወበቅ አንዱ ነው። በኤፕሪል የሶስተኛው አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም በጋምቤላ፣ በአፋር፣ በሶማሌ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝና በምዕራብ አማራ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ከ35 እንዲሁም በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከ40 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8) ።





ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 21-30, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.4 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በሜይ ወር ወቅታዊው ዝናብ ቀስ በቀስ ከበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየቀነሰ በመሄድ ከክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች መጠናከር ጋር ተያይዞ ዝናቡ ወደ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው፡፡

በመጪዎቹ የሜይ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በሜይ የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ስፍራዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸውና በተለይም የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን የሚገባው ዕርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የተሻለ የደመናና የዝናብ ሥርጭት በደቡባዊው አጋማሽ፤ በመካከለኛው እና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 9)፡፡




ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## 2.5 እ.አ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የሚጠበቀው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ይጠበቃል። በመሆኑም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በመጪው የኤፕሪል የመጨረሻ አስር ቀናት የሚኖረውን የእርጥበት ሁኔታ አልቆ ለመጠቀም ከታች ያሉትን የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የመኸር እርጥበት ተጠቃሚ ዞኖች** | | | | |
| ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ እና የመካከለኛዉ ጎንደር ዞኖች፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ ዞኖች የሰሜን እና የምዕራብ ጎንድር፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን መዕራብ ትግራይ ዞኖች የመካከለኛዉ እና የምስራቅ ዞኖች<br>የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ እና የመካከለኛዉ ጎንደር ዞኖች፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ ዞኖች የሰሜን እና የምዕራብ ጎንድር፣ ዋግ ህምራ | ከቀላል እስከ ከባድ እርጥበት | • የመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ ቀድመው የማሳ ዝግጅት ለማከናወን<br>• የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል<br>• ለቋሚ ሰብሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት<br>• ለደጋፊ የመስኖ ስራ በቂ የውኃ አቅርቦት | • የትነት መጠን መጨመር የአፈር ውስጥ እርጥበትን ሊቀንስ ይችላል<br>• የደረቅ ሰሞናት መኖር<br>• የእርጥበት መብዛትን በማይቋቋሙ የአፈር ጠባይ ያላቸው ማሳዎች መጨቅየት እና የውኃ መተኛት<br>• የአረም መብዛት የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት | • የእርጥበት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የአፈርና የውሃ እቀባ ስራ ማከናወን<br>• የእርጥበት መብዛት በሚያጠቃቸው አካባቢዎች ወኃን ከማሳ ለማንጣፈፍ ቅድመ ዝግጅት ማደረግ<br>• የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>• የጸረ አረም እና ተባይ ቅድመ መከላከል ዝግጅት ማድረግ |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| የሰሜን፤ የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ከፋ፣ ኤረር፣ ጃራር ፋፈን ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የማሳ ዝግጅት ለማድረግ<br>• ዘር ለመዝራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የሚኖረው እርጥበት ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን<br>• ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>• ከፍተኛ ትነት መኖር | • በተለያዩ ምክንያቶች ዘር ለመዝራት የዘገዩ አካባቢዎች ዘር ለመዘራት የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ<br>• የአፈርና የውሃ እቀባ ማከናወን<br>• የደጋፊ መስኖ የዝናብ ውሃ ማሰባሰብ<br>• በሰብል ማሳ የውሃ መከተር ማከናወን |



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

| በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ነጎብ፣ እና ዶሎ ዞኖች ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ አማሮ፣ ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሌ፣ ባስኬቶ፣ አሪ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የማሳ ዝግጅት ለማድረግ<br>• ዘር ለመዝራት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት<br>• የዝናብ ውኃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም | • ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት<br>• የአፈር መሸርሸር | • የተገኘውን እርጥበት በመጠቀም በደጋማ አካባቢዎች ዘር መዝራት<br>• ለእንስሳት መኖ የሚሆኑ ዝርያዎችን ከወዲሁ ማዘጋጀት<br>• የአፈርና የውሃ እቀባና የእርከን ስራ ማከናወን |

## 2.6 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውኃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኤፕሪል ሶስተኛው አስር ቀናት የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ያገኛሉ። ይህ ሁኔታ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር ውኃ ሀብት መጠን ያሻሽላል። ስለሆነም የሚገኘው እርጥበት በተገቢው ሁኔታ አልቆ ለመጠቀም ከታች ያሉትን የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦችን በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+2511155383 94ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ

| የውኃ ተፋሰሶች | የሚጠበቀው የእርጥበት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| አብዛኛው ገናሌ ዳዋ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ እንዲሁም የላይኛው ዋቢ ሸበሌ | ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል<br>• የመጠጥ ወኃ አቅርቦተ መሻሻል<br>• የመስኖ እና የሀይል ማመንጫ ግድቦች የውኃ ከፍታ መሻሻል | • ቅፅበታዊ ጎረፍ ውኃ ወለድ በሽታዎች ስጋት | • የፍሳሽ መውረጃዎች ማፅዳት<br>• ውሃን ከብክለት መከላከል<br>• የጎርፍ መውረጃዎች ማጽዳት<br>• የመጠጥ ውኃን አክሞ መጠቀም<br>• በወንዝ ዳርቻ የሚኖሩ ግንዛቤ መስጠት ወይም ማስተጠንቀቅ<br>• የአየር ሁኔታ ትንበያንና ሙያዊ ምክረ ሀሳብን መከታተል<br>• ወራጅ ውሃን ለማቋረዋ አለመሞከር<br>• |
| በአብዛኛው አዋሽ፣ባሮ አኮቦ ተከዜ ፣በመካከለኛ እና ታችኛው አባይ፣ | ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ እርጥበት | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል | • ከፍተኛ ትነት<br>• በቂ የውሃ ክምችት በሌለበት አካባቢ በተለይም አርብቶ አደር በእንስሳት በውሃ መጋጨት | • የዝናብ ውኃ የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ማሰባሰብ እና ማጠራቀም<br>• የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል ማስተዳደር<br>• የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ተግባራትን ማከናወን |
| በአይሻ፣ አፋር ደናከል እና የመረብ ጋሽ ንዑስ ተፋሰሶች | ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ | ምንጮች እና ሌሎች የውሃ አካላት ዉሃ ከጎርፍ ነፃ መሆን | • የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት መቀነስ | • የውኃ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የውኃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ<br>• የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>• የመጠጥ ውኃን አክሞ መጠቀም |



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et